# ለእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች

## ለአማካኝ ግዜ የሚሠራና ለአጭር ጊዜ የሚሠራ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች

| ዘዴ | የእርግዝና መከላከያ መርፌ<br>Depo-ProveraTM ወይም Depo – Ralovera, (እንዲሁም “ደፖ/depo” በሚል ይጠራል)<br> | በሴት ብልት ላይ ቀለበት<br> | በአፍ የሚወሰድ የእርግዝና መከላከያ ሁሉን ያካተተ ክኒን<br> | አነስተኛ ክኒንl<br> |
|---|---|---|---|---|
| **ውጤታማነት*** | • 94% | • በትክክል መጠቀም: 99%<br>• በመደበኛ መጠቀም: 93% | • በትክክል ከተጠቀሙ: 99%<br>• መደበኛ አጠቃቀም: 93% | • በትክክል ከተጠቀሙ: 99%<br>• መደበኛ አጠቃቀም: 93% |
| **ይህ ምንድ ነው?** | • መርፌ በሀኪም ወይም በነርስ ይሰጣል።<br>• ፕሮጀስትሮን የሚመስል ሆርሞን የያዘ<br>• በማህጸን መከፈቻ ላይ ወፈር ያለ ፈሳሽ በመፍጠር የወንዱ ስፐርም ከመግባት ያቆመዋል። | • ‘ለሁሉም የሚሆን አንድ ዓይነት መጠን’ ያለው ቀለበት ሲሆን በሴት ብልት ውስጥ ማስቀመጥ<br>• ከሴት ብልት ቀስ ብሎ ሆርሞንስ ይወጣና ወደ የደም መስመር በመንቀሳቀስ እርግዝናን ይከላከላል።<br>• በየ አራት ሳምንታት ይቀየራል (የወር አበባዎ በቆመ ከአንድ ሳምንት በኋላ)። | • በሀኪም የታዘዘ ሰው ሰራች ሆርሞኖች።<br>• እንቁላል ማምረትን በማቆም እንዲሁም በማህጸን መከፈቻ ላይ ወፈር ያለ ፈሳሽ በመፍጠር የወንዱን ስፐርም ከመግባት ያቆመዋል። | • በሀኪም የሚታዘዝ ሰው ሰራሽ አንድ ሆርሞን የያዘ<br>• በማህጸን መከፈቻ ላይ ወፈር ያለ ፈሳሽ በመፍጠር የወንዱ ስፐርም ከመግባት ያቆመዋል። |

VICTORIA
State Government
Health and Human Services

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል?** | • **ለአማካኝ ጊዜ የሚሠራ -** በእያንዳንዱ ወሲባዊ ግንኙነት በሚፈጽሙበት ጊዜ ማስታወስ አይኖርብዎትም<br>• ከ12 እስከ 14 ሳምታት ሉቆያል | • **ለአማካኝ ጊዜ የሚሠራ -** በእያንዳንዱ ወሲባዊ ግንኙነት በሚፈጽሙበት ጊዜ ማስታወስ አይኖርብዎትም<br>• ከሶስት ሳምንታት በኋላ ቀለበቱን ይወጣና ከአንድ ሳምንት በኋላ ቀለበት ይገባል። | • **ለአጭር ጊዜ የሚሠራ -** በየቀኑ ማውጣት እንዳለብዎት ማስታወስ አለብዎ | • **ለአጭር ጊዜ የሚሠራ -** በየቀኑ በተመሳሳይ ጊዜ ለማውጣት መርሳት የለብዎም። |
| **ጥቅሞች** | • እርስዎ ይህን ስለመጠቀምዎ ማንም ሰው መናገር አይችልም።<br>• ጡት እያጠቡ መጠቀም ይቻላል።<br>• በሌላ መድሃኒቶች ተጽእኖ ችግር አይፈጥሩበትም።<br>• የርስዎ ወር አበባ ቀላል ወይም ሊቆም ይችላል። | • ይህን በራስዎ ማስገባትና ለማስቀመጥ እንደ ሞዴስ መቀየር ቀላል ነው።<br>• የወር አበባን ቀላልና አነስተኛ ህመም እንዲኖር ያደርጋል።<br>• በርስዎ ዘር ማፍራት ላይ ችግር አይፈጥርም። | • የወር አበባን ለማሳለፍ ሊጠቅም ይችላል። | • በጤና ሳቢያ ኦስትሮጀን/oestrogen መውሰድ ለማይችሉ ሴቶች ተስማሚ ነው።<br>• ጡት በሚያጠቡበት ጊዜ መጠቀም ይቻላል። |
| **ሌላ ግምት ውስጥ የሚገባ** | • በየ 12 እስከ 14 ሳምንታት ሌላ መርፌ መውሰድ እንዳለብዎ ማስታወስ አለብዎት፤ አለበለዚያ ውጤቱ ይቀንሳል።<br>• መጠቀም ካቆሙ ብኋላ ወደ መደበኛ የወር አበባ ለመመለስ እና ለማርገዝ ጥቂት ወራት ሊወስድ ይችላል።<br>• በአጥንት ጥንካሬ ላይ ድከመትን ሊፈጥር ይችላል። | • የልብ በሽታ ችግር ካለብዎት፤ ለምሳሌ እድሜያቸው ከ35 ዓመት በላይ ለሆና ለሚያጨሱ ሰዎች አይመከርም። | • ኢንዶሜትሪያል እና ኦቫሪያን ነቀርሳ ስጋትን ሊቀንስ ይችላል። | • እንደ ተዋሃደ ክኒን ውጤታማ ላይሆን ይችላል፤ ምክንያቱም በተመደበለት ጊዜ ብቻ መወሰድ ስላለበት ነው።<br>• አንዳንድ ችግሮች ሊፈጥር ይችላል። |
| **ይህን ማን ሊጠቀም ይችላል?** | • ጡት የሚያጠቡ አስተማማኝ ሲሆን ነገር ግን የልጅዎ እድሜ ከስድስት ወር በታች ከሆነ የጡት ወተቱ መጠን ሊቀንስ ይችላል። | • ከወሊድ ከ21 ቀናት በኋላ መጠቀም ይቻላል። | የልብ በሽታ ችግር ካለብዎት፤ ማለት እድሚያቸው ከ35 ዓመት በላይ ለሆና ለሚያጨሱ ከሆነ እንዲወስዱ አይመከርም። | አንዳንድ የህክምና ሁኔታዎች ባሉበት (ማለት እንደ የጡት ነቀርሳ) ተስማሚ አይደለም። |

* በትክክል መጠቀም = እንደሚፈለገው በትክክል ሲጠቀሙ።

* በመደበኛ መጠቀም = በአግባቡ ሳይጠቀሙ።

**ለበለጠ መረጃ**

በወሲባዊ ግንኙነት ለሚተላለፉ ኢንፌክሽን በሽታዎች (STIs) መከላከያ ኮንዶም ብቻ ነው።

በቪክቶሪያ መንግሥት ሥልጣን ያገኘና የታተመ፤ አድራሻ 1 Treasury Place, Melbourne.
© State of Victoria, የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፤ January 2019.
በድረገጽ <http://healthtranslations.vic.gov.au/> ላይ ቀርቧል።